# የጡት ነቀርሳ ቀዶ ጥገና

ሁለት አይነት ዋና ዋና የጡት ነቀርሳ ቀዶ ጥገና አለ። አብጠቱን ማስወገድና ሙሉ ጡቱን ማስወገድ

ማስቴክቶሚ፣ ጡትን ለማስወገድ የሚደረግ ቀዶ ጥገና ነው። የጡት ነቀርሳን ለማከም ወይም ለመከላከል የሚፈጸም ነው። ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጡ በሽተኞች ብቻ ናቸው ነቀርሳን ለመከላከል የቀዶ ጥገና የሚያደርጉ።



ነቀርሳን መፍራት የተለመደ ባሕሪ ነው። የጡት ነቀርሳ፣ አስቀድሞ ከታወቀ፣ ሊታከም የሚችል ነው።

አራት ዋና የቀዶ ጥገና ዓይነቶች አሉ፤

- **ላምፔክቶሚ** - እብጠቱን (ጡቱን ሳይሆን) ብቻ ለማስወገድ የሚደረግ ቀዶ ጥገና ነው። በእብጠቱ ጫፎች ላይ ያሉትን የነቀርሳ ሴሎችን ለማስወገድ ሲባል፣ በእብጠቱ አጠገብ ያለውን አነስ ያለ የስጋ መጠን አብሮ ይነሳል።
- **አጠቃላይ ማስቴክቶሚ** - የጡትን ጫፍ ጨምሮ፣ የታመመውን ጡት ማስወገድ
- **የተሻሻለ ልዩ ማስቴክቶሚ** - ጡትን፣ በብብት ስር ያሉትን አንዳንድ ሊንፍ ኖዶችንና፣ በደረት ጡንቻዎች ላይ ያለውን ሽፋን ለማስወገድ
- **ልዩ ማስቴክቶሚ** - ጡትን፣ ሊንፍ ኖዶችንና የደረት ጡንቻዎችን ማስወገድ። ይህ ዓይነት ቀዶ ጥገና ዘወትር የሚፈጸም አይደለም።

ለጡት ነቀርሳ የሚፈጸመው ቀዶ ጥገና እንደ ነቀርሳው ያለበት ደረጃ፣ የነቀርሳው ትልቅነት፣ የጡቱ ትልቅነትና፣ በብብት ስር ባሉት ሊንፍ ኖዶች ውስጥ የነቀርሳ ሴሎች መኖራቸውንና አለመኖራቸውን ታይቶ የሚወሰን ነው።



ሊንፎ ኖዶች፣ ኢንፌክሽንን ለመከላከልና እንደ የነቀርሳ ሴሎችንና ባክቴሪያዎችን የመሳሰሉ ያልተፈለጉ ነገሮችን በማጣራት የሚረዱ የሊንፋቲክ ሲስተም ክፍል ነው። በሊንፍ ኖዶች ውስጥ ታፍነው የተያዙ የነቀርሳ ሴሎች ሊያድጉ ይችላሉ።

የሚያደርጉት ቀዶ ጥገና የሚወሰነው እርስዎና ሐኪምዎ የቀበሉት ወይም አይቀበሉትም እንደሆነ ታይቶ ነው። አብዛኛዎቹ ሴቶች ቀዶ ጥገና ከማድረጋቸው በፊት የሁለተኛ ሐኪምን አስተያየት ይጠይቃሉ።

የጡት ዳግመ ግንባታ፣ አንዲት ሴት ማስቴክቶሚ ከፈጸመች በኋላ የጡትዋን ቅርጽ ዳግመኛ ለመገንባት ልታደርገው የምትችል የቀዶ ጥገና ሂደት ነው። ዳግመኛ የተገነባ ጡት እንደ በተፈጥሮ የነበርዎት ጡት ስሜት የለውም። ቢሆንም የጡት ዳግመኛ ግንባታ ያደረጉ አብዛኛዎቹ ሴቶች፣ ቀዶ ጥገናውን በማድረጋቸው ደስተኞች ናቸው።

የቀዶ ጥገና ሃኪም በብዙ መንገድ የጡት ዳግም ግንባታ ማድረግ ይችላል ። አንዳንድ ሴቶች ጡት ማስተከል ይመርጣሉ እሱም በሳሊን ወይም በሲሊኮን ጀል መሙላት ነው።



የቀዶ ጥገና ሃኪም በብዙ መንገድ የጡት ዳግም ግንባታ ማድረግ ይችላል ። አንዳንድ ሴቶች ጡት ማስተከል ይመርጣሉ እሱም በሳሊን ወይም በሲሊኮን ጀል መሙላት ነው።

ሌላው ዘዴ ደግሞ ከሌላ የሰውነት ክፍል በምውሰድ ይሆናል። የቀዶ ጥገና ሃኪም ቆዳ ጡንቻ እና ጮማ ከሆድ ዝቅ ብሎ ካለው አካል ከጀርባ ወይም ከመቀመጫ ላይ በመውሰድ ይሆናል

የጡት ዳግመ ግንባታ፣ ማስቴክቶሚውን ከፈጸሙ በኋላ ወዲያዉኑ ወይም በሌላ ግዜ ሊፈጸም የሚችል ነው። ለእርስዎ የተሻለው ምርጫ የቱ እንደሆነ ለማወቅ ሐኪምዎን ያናግሩ።

ያልዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎችን ወይም ሐሳብ አስመልክቶ ከጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጭዎ ጋር ይወያዩ።

**A project by Health Roads Media and EthnoMed**
This project has been funded in whole or in part with Federal funds from the Department of Health and Human Services, National Institutes of Health, National Library of Medicine, under Contract No. HHS-N-276-2011-0008-C with the University of Washington.
Thank you to Safeway Foundation for its support to Harborview Medical Center's EthnoMed for the development of cancer-related content.